<u>የኢትዮጵያ ጠለፋ መድን አክስዮን ማህበር የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ (ማሻሻያ ቁጥር 1)</u>

አንቀጽ 1፡ ያማሻሻያው ዓላማ

የዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻያ ዓላማ በአሁኑ ጊዜ የፋይናንስ ሥራን በተመለከተ በሀገራችን ዘርፈ-ብዙ ለውጦች በመደረግ ላይ በመሆናቸው፤ በተለይም የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 መውጣቱን ተከትሎ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) ተቋቋመው ስራ በመጀመራቸውና ይህንን ተከትሎም እንደ አክሲዮን ያሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች (Securities) አወጣጥ፣ ምዝገባና ግብይትን በተመለከተ አዳዲስ ህጎች፣ መመሪያዎች እና አሰራሮች በመውጣታቸው ቀደም ሲል የነበረውን የአክሲዮን ማህበሩን የመመስረቻ ጸሁፍ ከአዲሶቹ ህጎች፣ መመሪያዎች እና አሰራሮች ጋር እንዲጣጣም አድርጎ ለማሻሻል እንዲሁም ሌሎች ማሻሻያዎችንም ማድረግ በማስፈለጉ ነው። ስለሆነም የመመስረቻ ጽሁፍ እንደሚከተለው ተሻሽሎ ታህሳስ 14 ቀን 2018 ዓ/ም በተደረገው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች 5ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጽድቋል።

አንቀጽ 2፤ የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

(1) የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚገኘው በኢትዮጵያ፡ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ --- የቤት ቁጥር አዲስ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

(2) ማህበሩ እንደ አስፈላጊነቱ ተቀጥላ፣ ሆልዲንግ ወይም ግሩፕ ኩባንያዎችን ማቋቋም ይችላል።

አንቀጽ 3፤ የማህበሩ የስራ መስክ እና ዓላማ

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) በኋላ፣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ "ሐ" እና "መ" ተጨምረዋል።

ሐ. በስራ ላይ ባሉ የካፒታል ገበያ ሕጎች መሠረት የተለያዩ ዓይነት ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን ማውጣት።

መ. በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድና ቁጥጥር ህጎችና መመሪያ መሰረት በካፒታል ገበያ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተቀጥላ ኩባንያ አማካኝነት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ሆኖ መስራት፤

አንቀጽ 4: የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል እና የተከፈለ የገንዘብ መጠን

በአ/ማህበሩ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 አሁን ባለው የዋና ገንዘብ/ካፒታል እና የተከፈለ የገንዘብ መጠን መሰረት የተሻሻለ ሲሆን አንቀጽ 2 ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝ ተደርጓል። ስለሆነም አንቀጽ 6 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

“የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር 000 ( ) ሆኖ ይኸውም የነጠላ ዋጋቸው ብር 10,000 (አስር ሺህ) በሆኑ () አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው። የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ ብር 000 ( ) ነው።”

አንቀጽ 5፡ አክስዮን የሚወጣባቸው ዘዴዎች

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 8 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

በማህበሩ የሚወጡት አክስዮኖች/ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ በሆነ መልክ ይወጣሉ። አፈጻጸሙ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ይፈጸማል።

አንቀጽ 6፤ የባለአክስዮኖች መዝገብ

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 10 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የአክሲዮን ባለቤትነት መዝገቦች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚዘጋጅ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚመዘገብበት የሂሳብ መዝገብ ስርዓት ተመዝግበው ይያዛሉ።
2. በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአ/ማህበሩ ዋና መ/ቤት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ጾታ፣ የተፈረሙ እና የተከፈሉ አክሲዮኖችን ብዛትና እና የገንዘብ መጠን እንዲሁም ድምጽ የመስጠት መብትን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይኖራል።

አንቀጽ፤ 7 የአክስዮን ማስረጃ

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 11 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የአክስዮን ጥበቃ፣ ምዝገባ እና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በካፒታል ገበያ አዋጁ እና አዋጁን ተከትለው በወጡ መመሪያዎች መሰረት ይፈጸማል።

አንቀጽ 8፤ የአክስዮን መተላለፍ

የመመስረቻ ጸሁፉ አንቀጽ 12 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የማህበሩ አክስዮኖች በተቆጣጣሪው አካል መመሪያ እንዲሁም በካፒታል ገበያ ህግና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ሊተላለፉ ይችላሉ።
2. አክሲዮኖችን የማስተላለፍ ተግባር በማህበሩ ላይ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ዝውውሩ በሕግ አግባብ ሲደረግና ሲመዘገብ ነው።

አንቀጽ 9፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን፣ ሀላፊነት እና ተጠያቂነት

የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ከ(ሀ) - (ጀ) ያሉት እንደተጠበቁ ሆኖ አዲስ ንዑስ አንቀጾች (ገ)፣ (ጠ)፣ (ጨ)፣ (ጰ)፣ (ጸ)፣ (ፀ) እና (ፈ) አሁን ካለው ንዑስ አንቀጽ (ጀ) በታላ ተጨምረዋል፡፡

(ገ). በሥራ ላይ ባሉ ህጎችና ደንቦች መሠረት የማህበሩን ካፒታል በቀጥታ የማይጨምሩ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለገበያ ማቅረብ ላይ ውሳኔ ለመስጠት፤

(ጠ) የማህበሩን ማንኛውም ሠነደ ሙዓለ ንዋይ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን ጨምሮ በተቆጣጣሪ የመንግስት አካላት፥ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ዘንድ የሚመዘገብበትን ወይም ለሽያጭ የሚቀርብበትን ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ ለመቆጣጠር፥ ለመጀመር እና ለመወሰን፤

(ጨ). የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች ወይም አግባብነት ያለው ተቋም በሚያዘው መሰረት የካፒታል ገበያ መስፈርቶችን፥ የማሳወቅ ግዴታዎች፣ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች፣ እና የማህበሩ አስተዳደር ግዴታዎች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እየተከበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

(ጰ) ለማህበሩ በካፒታል ገበያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊ የሆኑትን ወይም ተያያዥነት ያላቸውን ሁሉንም እርምጃዎች ለመውሰድና ተግባራትን ለመወከል፣ ይህም በተቆጣጣሪ አካላት ፊት መቅረብን፣ የሚያስፈልጉ ሠነዶችን መደራደርና መፈረምን፥ እና የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን በማክበር የካፒታል ገበያ ስትራቴጂዎችን መተግበርን ያጠቃልላል፤

(ጸ) ማህበሩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ እንዲያገኝ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ሕጋዊ እርምጃዎች ለመውሰድ፤

(ፀ)ማህበሩ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንዲሆን ወይም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት አባል እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ሕጋዊ እርምጃዎች ለመውሰድ፤

(ፈ) ማህበሩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ሆኖ ለመስራት የሚያስችል ፈቃድ አኒኝቶ በካፒታል ገበያ ተግባራት ላይ ለመሰማራት ሲል ንዑስ ኩባንያ ለማቋቋም ወይም ቀደም ሲል በተቋቋሙ ወይም አዲስ በሚቋቋም ተቀጥላ ኩባንያ ውስጥ የአክስዮን ድርሻ ለማግኘት ለመወሰንና ሁሉንም ሕጋዊ እርምጃዎች መውሰድ፤

አንቀጽ 10፤ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

የመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 45 መግቢያው ብቻ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

“አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በተቆጣጣሪው አካል መመሪያዎች ላይ የተደነገጉት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የአ/ማህበሩ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡”

አንቀጽ 11፤ ማስታወቂያዎች እና ምዝገባዎች (ድረ-ገጽ)

የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

(2) በድረ-ገጹ የሚገለጹት ዝርዝር መረጃዎች በንግድ ህጉ አንቀጽ 493፣ በካፒታል ገበያ ህግ እና መመሪያዎች የተመለከቱት ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ህግ የተመለከቱት ወይም አክሲዮን ማህበሩ ሊገለጹ ይገባል ብሎ ያመነባቸው ሌሎች መረጃዎች ናቸው፡፡

አንቀጽ 12፤ አንቀጽ 55 ሆኖ የተጨመረ አዲስ ድንጋጌ፤ ስለ አዳዲስ ሕጎችና መመሪያዎች

የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ አንቀጽ 55 ሆኖ እንዲገባ እና ነባሩ አንቀጽ 55 ደግሞ አንቀጽ 56 ሆኖ እንዲነበብ ተደርጓል፡፡

“ይህንን የመመሥረቻ ጽሑፍ የሚያሻሽሉ፣ የሚሽሩ ወይም የሚቃረኑ ሕጎችና መመሪያዎች ቢወጡ ሕጎቹ ይህ የመመስረቻ ጽሑፍ እንዲሻሻል ካላስገደዱ በስተቀር የመመሥረቻ ጽሑፉን ማሻሻል ሳያስፈልግ ሕጎቹና ደንቦቹ ተፈፃሚ ይሆናሉ።”